https://chilot.me

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ሁለተኛ ዓመት ቁጥር ፳፱
አዲስ አበባ ጥር ፳፯ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

22nd Year No.29
ADDIS ABABA 5th February 2016

## ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፫፻፸፩/፪ሺ፰ ዓ.ም

የወንጀል ምስክሮች የውሎ አበልና የጉዞ ወጪ አከፋፈል የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ……………..… ገጽ ፰ሺ፯፻፷፬

## CONTENT

Regulation No.371/2015

Payment of Per diem and Transportation Cost of Witnesses Criminal Offences Council of Ministers Regulation ....Page 8764

የሚኒስትሮች ምክር ደንብ ቁጥር ፫፻፸፩/፪ሺ፰

**ስለወንጀል ምስክሮች የውሎ አበልና የጉዞ ወጪ አከፋፈል የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፱፻፲፮/፪ሺ፯ አንቀጽ ፭ እና በወንጀል ምስክሮችና ጠቋሚዎች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር ፮፻፺፱/፪ሺ፪ አንቀጽ ፴፩ (፩) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

፩. **አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የወንጀል ምስክሮች የውሎ አበልና የጉዞ ወጪ አከፋፈል የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፸፩/፪ሺ፰" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩/ "የፍትህ አካል" ማለት በሕግ ወንጀል የመመርመር፣ የወንጀል ክስ የማቅረብ ወይም ክስ በመስማት ፍርድ

**COUNCIL OF MINISTERS REGULATION No.371/2015**

**COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR THE PAYMENT OF PER DIEM AND TRANSPORTATION COST OF WITNESSES OF CRIMINAL OFFENCES**

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 916/2015 and Article 31(1) of the Protection of Witnesses and Whistleblowers of Criminal Offences Proclamation No. 699/2010.

## PART ONE

## GENERAL

1. **Short Title**

This Regulation may be cited as the "Payment of Per diem and Transportation Cost of Witnesses of Criminal Offences Council of Ministers Regulation No. 371/2015''.

2. **Definitions**

In this Regulation, unless the context otherwise requires:

1/ "justice organ" means any federal government organ duly authorized to perform crime investigation by law, prosecute cases or give

https://chilot.me



የመስጠት ሥልጣን ያለው ማንኛውም የፌደራል ፹ሺ፯፻፷፭ ት አካል ነው፤

፪/ “የፍትህ አካል የበላይ ኃላፊ” ማለት እንደፍትህ ተቋሙ አግባብነት ዋና ኃላፊ ሲሆን ምክትሎችን ይጨምራል፤

፫/ “የክፍያ መጠየቂያ ቅፅ” ማለት የወንጀል ምስክር የውሎ አበል እና የጉዞ ወጪ እንዲከፈለው የሚሞላበት ቅፅ ነው፤

፬/ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው የሴትንም ፆታ ይጨምራል፡፡

## ፫. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ ደንብ የደንብ መተላለፍ ጉዳዮችን ሳይጨምር በፌደራል ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ስልጣን ሥር በሚታይ የወንጀል ጉዳይ ላይ በምርመራ፣ በክስ ወይም በክስ መስማት ሂደት ማስረጃ ወይም ምስክርነት እንዲሰጥ በቀረበ ምስክር ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።

## ክፍል ሁለት
## ስለውሎ አበልና የጉዞ ወጭ አከፋፈል

## ፬. የፍትሕ አካላት ኃላፊነት

፩/ ማንኛውም የፍትህ አካል ለጠራው የወንጀል ምስክር በዚህ ደንብ መሠረት የውሎ አበልና የጉዞ ወጪ ይሸፍናል፤

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም ይህ ደንብ በሚከተሉት ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፦

ሀ) በወንጀል ሕጉ እና በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕጉ መሠረት በግል አቤቱታ ክስ እንዲቀርብ በተፈቀደባቸው መዝገቦች ተጠርተው ለሚቀርቡ ምስክሮች፤

ለ) ፍትሕ አካል ዘንድ ለመመስከር ቀርቦ የምስክርነት ቃሉን ለመስጠት ፈቃደኛ ላልሆነ የወንጀል ምስክር፤

ሐ) ከሥራው ጋር በተያያዘ ኃላፊነቱን ወይም የሙያ ግዴታውን በሚወጣ የመንግስት ሠራተኛ፤

judgment upon hearing;

2/ “head of justice organ” means the principal including the deputy heads, as relevant to justice organ;

3/ “payment request form’’ means leaflet filled by witnesses of criminal offences for the request of per diem and transportation cost;

4/ any expressions in the masculine gender includes the feminine.

## 3. Scope of Application

This Regulation shall, except the petty offences, be applicable to a witness who appears for provision of evidence or testimony in the process of investigation, prosecution or adjudication of a criminal offence that falls under the jurisdiction of federal courts.

## PART TWO
## Payments Of Per Diem And Transportation Cost

## 4. Responsibility of Justice Organs

1/ Any justice organ shall, in accordance with this Regulation, cover per diem and transportation cost of a witnesses summoned by it;

2/ Notwithstanding the provision of sub-article (1) of this Article, this Regulation shall not be applicable to:

a) a witness criminal offence that appears for provision of evidence or testimony for crimes punishable upon complaint as provided for under the Criminal Code and the Criminal Procedure Code;

b) a witness of criminal offence who appears before justice organ to provide testimony but unwilling to testify;

c) public servant who performs his professional duty or responsibility in relation to his occupation;

d) a witness of criminal offence suspected of

https://chilot.me



መ) በሐሰተኛ ምስክርነት የተጠረጠረ የወንጀል ምስክር ፤ ወይም

፹ሺ፯፻፰፯

, .. . ከሳሽ መከላከያ ምስክር፡፡

## ፭. ስለ ውሎ አበል አከፋፈል

ለወንጀል ምስክር የሚከፈለው የውሎ አበል፦

፩/ ምስክሩ በማንኛውም አሠሪ ተቀጥሮ የሚሰራ ሠራተኛ ከሆነ በወር ደመወዙ ላይ ተመሥርቶ በመንግስት ሠራተኞች የውሎ አበል አከፋፈል መመሪያ መሠረት ተሰልቶ ይከፈለዋል፤ ወይም

፪/ ምስክሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ተቀጥሮ የሚሰራ ሠራተኛ ካልሆነ በመንግስት ሠራተኞች የውሎ አበል አከፋፈል መመሪያ የተመለከተው መካከለኛው የውሎ አበል መጠን ይከፈለዋል፡፡

## ፮. ስለ ጉዞ ወጪ አከፋፈል

፩/ ለወንጀል ምስክር የሚከፈለው የጉዞ ወጪ መጠን የሕዝብ ማመላለሻ የአንድ ጉዞ የትራንስፖርት ታሪፍ በሁለት ተባዝቶ የሚገኘው መጠን ይሆናል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም ምስክሩ የሕዝብ ማመላለሻ መጠቀም የማይችል ሲሆን እና የፍትህ አካሉ የበላይ ኃላፊ የግል ተሽከርካሪ እንዲጠቀም ከፈቀደ ለነዳጅ ያወጣው ወጪ ይተካለታል፡፡

፫/ የወንጀል ድርጊቱ ያለምስክሩ ቃል በሌላ በማናቸውም መንገድ ሊረጋገጥ የማይችል ወይም ምስክርነቱ በአስቸኳይ ሊሰጥ የሚገባ ሲሆን እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) የተመለከተውን የመጓጓዣ መንገዶችን ለመጠቀም አመቺ በማይሆንበት ጊዜ በፍትህ አካሉ የበላይ ኃላፊ ፈቃድ የአየር መጓጓዣ የጉዞ ወጪ ለወንጀል ምስክሩ ይከፈላል፡፡

፬/ ለወንጀል ምስክር የሚከፈለው የጉዞ ወጪ የሚሰላው ለምስክሩ በተፃፈው መጥሪያ ላይ ከተገለጸው የመኖሪያ ወይም የሥራ አድራሻ አጭር ርቀት ላይ በመመስረት ይሆናል፡፡

false testimony; or

e) defense witness of the accused.

## 5. Payment of Per Diem

The amount of per diem to be paid to a witness of criminal offence shall be:

1/ calculated on the basis of his salary in accordance with the directive applicable for payment of per diem of public servants, if the witness is an employee of any undertaking; or

2/ the average per diem of civil servants as specified in the directive applicable for payment of per diem of public servants, if the witness is not an employee pursuant to sub-article (1) of this Article.

## 6. Payment of Transport Cost

1/ The amount of transportation cost to be paid to a witness of criminal offence shall be twice of the tariff paid for one trip public transportation.

2/ Notwithstanding sub-article (1) of this Article, if the witness of criminal offence is unable to use public transport and the head of justice organ permits the use of private vehicle, he shall be refunded the fuel expense incurred.

3/ When the crime cannot be proved otherwise than the testimony of the witness or the testimony is sought be given urgently and where the uses of the means of transportation specified under sub-articles (1) and (2) of this Article are not convenient, a flight cost shall be paid upon the approval of the head of the justice organ.

4/ The amount of transportation cost to be paid to a witness of criminal offence shall be calculated on the basis of the shortest distance from the residential or occupational address specified on the summon.

https://chilot.me



፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) መሠረት ምስክሩ እንዲቀርብ በተጠራበት መጥሪያ ላይ የተገለፀው
፹፯፻፷፯ ወይም የሥራ አድራሻ ትክክለኛ ባለመሆኑ በጉዞ ወጭ አከፋፈል ላይ ተጽዕኖ የሚያመጣ ከሆነ ይኸው እንዲታረም ለፍትህ አካሉ ማመልከቻ ማቅረብ ይችላል፡፡

፮/ ማንኛውም የወንጀል ምስክር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩)፣ (፪) ወይም (፫) መሠረት ያወጣው ወጪ እንዲተካለት በፍትህ አካሉ የተዘጋጀውን የክፍያ መጠየቂያ ቅጽ ሞልቶ ወጪውን ከሚያሳይ ደረሰኝ ጋር አያይዞ ማቅረብ አለበት፡፡

፯/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ(፮) የተደነገገው ቢኖርም የወንጀል ምስክሩ የወጪ ደረሰኝ ማቅረብ ያልቻለበት ምክንያት አሳማኝ ሲሆን በፍትህ አካሉ የበላይ ኃላፊ ውሳኔ በመንግሥት ሠራተኞች የጉዞ ወጪ አከፋፈል ሥርዓት መሠረት እንዲከፈለው ሊፈቀድ ይችላል፤ ሆኖም የወንጀል ምስክሩ በራሱ በሆነ ጥፋት የወጪ ደረሰኝ ማቅረብ ካልቻለ ክፍያው አይፈፀምም፡፡

፯. <u>ስለልዩ አዋቂ ምስክር የውሎ አበልና የጉዞ ወጪ አከፋፈል</u>

በዚህ ደንብ አንቀጽ ፬ (፪) (ሐ) ከተመለከተው ውጭ ያለ ሌላ የልዩ አዋቂ ምስክር፦

፩/ ለምስክርነት በቀረበ ጊዜ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፭ እና ፮ መሠረት የውሎ አበልና የጉዞ ወጪ ይከፈለዋል፤

፪/ በሚሰጠው የምስክርነት ጉዳይ ምክንያት የተለየ ወጪ ያወጣ እንደሆነ በሚያቀርበው ደረሰኝ መሠረት ወጪው ይተካለታል፡፡

፰. <u>ምስክርነት ሳይሰጥ የውሎ አበል እና የጉዞ ወጪ ስለመክፈል</u>

የወንጀል ምስክር ፍትሕ አካል ዘንድ ቀርቦ በራሱ ባልሆነ ምክንያት የምስክርነት ቃሉን ሳይሰጥ ቢቀርም የውሎ አበል እና የጉዞ ወጪ ይከፈለዋል፡፡

5/ When the residential or occupation address specified in summon pursuant to sub- article (4) of this Article is incorrect and has a prejudice on the payment of transport cost, the witness may apply to the justice organ for correction of such mistake.

6/ Any witness shall apply for the reimbursement of the cost incurred pursuant to sub-article (1), (2) or (3) of this Article attached with a filled payment request form and receipt of cost incurred.

7/ Notwithstanding to sub-article (6) of this Article, if the witness cannot produce receipt of payment for transport cost, a payment in accordance with public servants transportation cost payment system may be effected when substantiated by a convincing reason and approved by the head of justice organ; provided, however, that payment shall not be effected if receipt is not presented due to the fault of the witness.

**7. <u>Payment of Per Diem and Transportation Cost of Expert Witness</u>**

An expert witness otherwise than stipulated under Article 4 (2) (c) of of this Regulation shall be:

1/ paid per diem and transportation cost pursuant to Article 5 and 6 of this Regulation, when he appears as a witness;

2/ reimbursed an exceptional expense he incurred as a result of the testimony he provided on the basis of receipt he presents.

**8. <u>Payment of Per Diem and Transportation Cost without Providing Testimony</u>**

The per diem and transportation cost shall be paid to a witness who appears before justice organ and unable to provide testimony due to reasons not imputable to him.

https://chilot.me



**፱. <u>ስለ ቅድመ ክፍያ</u>**

፩/ ማንኛውም የወንጀል ምስክር ለምስክርነት በተጠራበት ጊዜ በገንዘብ እጦት ምክንያት ለመቅረብ የማይችል ፹ሺ፯፻፷፰ ከታመነ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፭ እና ፮ የተመለከቱት ክፍያዎች በቅድሚያ እንዲከፈሉት የሚመለከተው የፍትሕ አካል የበላይ ኃላፊ ሊፈቅድ ይችላል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚፈቀድ የቅድሚያ ክፍያ መጠን ከጠቅላላ ክፍያ ከግማሽ መብለጥ የለበትም፤ ሆኖም እንደነገሩ ሁኔታ በፍትሕ አካሉ የበላይ ኃላፊ ሲፈቀድ ከግምሽ በላይ የሆነ ክፍያ ሊከፈል ይችላል፡፡

**፲. <u>ስለ ምስክር ረዳት</u>**

፩/ በዕድሜ፣ በአካል ጉዳት ወይም በህመም ምክንያት ረዳት የሚያስፈልገውን የወንጀል ምስክር ለመርዳት አብሮ የተገኘ ረዳት ሰው በዚህ ደንብ አንቀጽ ፭ እና ፮ የተመለከቱት ክፍያዎች ይፈጸሙለታል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚቀርብ ረዳት ሰው ከአንድ መብለጥ የለበትም፤ ሆኖም የምስክሩ ሁኔታ ተጨማሪ ረዳት የሚጠይቅ መሆኑ በፍትህ አካል የበላይ ሃላፊ ከታመነ ተጨማሪ አንድ ሰው ሊፈቀድ ይችላል፡፡

**፲፩. <u>የክፍያ መጠየቂያ ቅጽን ሞልቶ ስለማቅረብ</u>**

፩/ ማንኛውም የወንጀል ምስክር እንዲሞላ የሚጠየቀውን የክፍያ መጠየቂያ ቅጽ በእውነትና በትክክል የመሙላት ግዴታ አለበት፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት በቅጽ ላይ የተሞላው መረጃ ትክክለኛ መሆኑን የሚመለከተው የፍትህ አካል የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት፡፡

**፲፪. <u>ሐሰተኛ የወንጀል ምስክር</u>**

9. **<u>Advance Payment</u>**

1/ The head of relevant justice organ may authorize advance payment of those payments stipulated under Article 5 and 6 of this Regulation, when it is believed that the witness is unable to appear in the time summoned because of financial constraints.

2/ The amount of advance payment to be effected pursuant to sub-article (1) of this Article shall not exceed half of the total amount; as the case may be, provided, however, that payment exceeding half of the total amount may be effected by the permission of the head of justice organ.

10. **<u>Assistant to a Witness</u>**

1/ An assistant person who appears to assist a witness of criminal offence that needs support because of age factor, disability or sickness, shall be entitled to payments stipulated under Article 5 and 6 of this Regulation.

2/ An assistant person to a witness of criminal offence who appears in accordance with sub-article (1) of this Article shall not be more than one; provided, however, that if the condition of the witness justifies additional assistance and the head of justice organ is convinced, one additional assistant may be permitted.

**11. <u>Filling and Submitting Payment Request Form</u>**

1/ Any witnesses of criminal offences shall have obligation to fill the payment request form truthfully and correctly.

2/ The relevant justice organ shall have responsibility to verify the correctness of information filled on the payment request form pursuant to sub-article (1) of this Article.

**12. <u>False Witness</u>**

Without prejudice to of Article 4 (2) (d) of this Regulation, if it is verified by the justice organ that a

https://chilot.me



በዚህ ደንብ አንቀጽ ፬ (፪) (መ) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የወንጀል ምስክር፦

፩/ ሐሰተኛ ምስክርነት በመስጠት መጠርጠሩን፣ ወይም

፹ሺ፯፻፷፱

፪/ ሆነ ብሎ ከፍተኛ አበል ወይም የጉዞ ወጪ ክፍያ ለማግኘት ሲል ሥራውን፣ የመኖሪያ አድራሻውን ወይም መሰል ጉዳዮችን በተመለከተ ሐሰተኛ መረጃ መስጠቱን፣

የፍትህ አካሉ ያረጋገጠ እንደሆነ የውሎ አበልና የጉዞ ወጭ ክፍያ አይፈጸምለትም፤ ተከፍሎትም እንደሆነ እንዲመልስ ይደረጋል፡፡

**፲፫. <u>የሌሎች ደንቦችና መመሪያዎች ተፈጻሚነት</u>**

በዚህ ደንብ ያልተሸፈኑ የወንጀል ምስክር የውሎ አበልና የጉዞ ወጪዎች አከፋፈልን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ አግባብ ያላቸው የፌደራል ሕጎች ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

**፲፬. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ጥር ፳፯ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**

**ጠቅላይ ሚኒስትር**

witness of criminal offence:

1/ is suspected for providing false testimony; or

2/ intentionally provides false information about his job, residence address and others similar facts with an intent to get higher payment;

The payment of per diem and transportation cost shall not be effected, if it is already paid up, it shall be returned back

**13. <u>Applicability of other Regulations and Directives</u>**

The relevant federal laws shall be applicable for a witness of criminal offence regarding matters related to payment of per diem and transportation cost which are not covered by this Regulation.

**14. <u>Effective Date</u>**

This Regulation shall enter into force on the date of their publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this day of 5th February, 2016**

**HAILEMARIAM DESSALEGN**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**